# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

# የህንጻ መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

# ቁጥር 09/2010

ግንቦት 2010 ዓ.ም

ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት

## መመሪያ ቁጥር 09/2010

## የህንፃ መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

የህንፃ መመሪያ ቁጥር 5/2003ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ በህንፃ ደንብ ቁጥር 243/2003 አንቀፅ 46 እና በህንጻ መመሪያው አንቀፅ 54 መሰረት ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የህንፃ መመሪያ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር 09/2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ማሻሻያ

የህንፃ መመሪያ ቁጥር 5/2003 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. የመመሪያው ክፍል 2 አንቀፅ 4 ስር ንዑስ አንቀፅ 4.4.12 ድንጋጌ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 4.4.12 ተተክቷል፦

4.4.12 ለሁሉም የህንፃ ምድቦች የህንፃውን ዲዛይን ወይም ፕላን ያዘጋጁ ባለሙያዎች ከዋናው ሰነድ የተመሳከረ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ ናቸው።

2. በመመሪያው ክፍል 2 አንቀፅ 4 ስር ከንዑስ አንቀፅ 4.8.8 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ 4.8.9 ተጨምሮ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በመያዝ ተካቷል፦

4.8.9 ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርቡ ዲዛይኖች ተሻሽለው ሥራ ላይ በዋሉ የኢትዮጵያ ሕንፃ ስታንዳርዶች መሰረት የተዘጋጁ መሆን አለባቸው፤

4.8.9.1 አርክቴክቸራል ዲዛይን

ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርብ አርቴክቸራል ዲዛይን ተሻሽሎ ሥራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ መሠረት መከናወን አለበት። ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑንና በስታንዳርዱ መሠረት መሰራቱን ያረጋግጣል።

4.8.9.2 የስትራክቸራል ዲዛይን

የሕንፃ ስትራክቸራል ዲዛይን ከመሠረት ሥራው ጀምሮ እስከ ጣሪያ ስራ በሥራ ላይ በዋሉት የሕንጻ ስታንዳርዶች መሠረት መከናወን ይኖርበታል።

ሀ) የሕንፃ ከመሠረት በታች እና በላይ ላሉ ስትራክቸራል ዲዛይኖች ተሻሽለው ሥራ ላይ በዋሉ የኢትዮጵያ ሕንፃ ስታንዳርዶች መሰረት የሚመለከታቸውን ክፍሎች እንደየ አስፈላጊነታቸው በአግባቡ ተጠቅሞ ዲዛይኑ መከናወኑን እና በዲዛይን ሪፖርት ውስጥም በዝርዝር



የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
የፖሊሲና ማህደር አገልግሎት

መካተታቸውን መታየት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑንና በስታንዳርዱ መሠረት መስራቱን ያረጋግጣል።

ለ) የሕንፃ ስትራክቸራል ዲዛይን በሚደረግበት ወቅት ሕንፃው የሚገነባበት አካባቢን እንደ አስፈላጊነቱ ተሻሽሎ ሥራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ መሰረት የመሬት መንቀጥቀጥ ከግምት ውስጥ በማስገባት መከናወን ያለበት ሲሆን በሪፖርት ውስጥም ክንውኑ በዝርዝር መታየት ይኖርበታል። ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑንና በስታንዳርዱ መሠረት መስራቱን ያረጋግጣል።

4.8.9.3 የሕንፃ ሳኒተሪ ዲዛይን

የሕንፃ ሳኒተሪ ዲዛይን ተሻሽሎ ሥራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ መሰረት ዲዛይኑ መከናወን ያለበት ሲሆን በሪፖርት ውስጥም በዝርዝር መታየት ይኖርበታል። እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑንና በስታንዳርዱ መሠረት መስራቱን ያረጋግጣል።

4.8.9.4 የኤሌትሪካል ዲዛይን

የሕንፃ ኤሌትሪካል ዲዛይን ተሻሽሎ ሥራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ መሠረት መከናወን አለበት። በሪፖርቱም ውስጥ በዝርዝር መታየት የሚኖርበት ሲሆን፤ ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑንና በስታንዳርዱ መሠረት መስራቱን ያረጋግጣል።

4.8.9.5 የመካኒካል ቬንቲሌሽን እና ኤር ኮንዲሽኒንግ ዲዛይን

የሕንፃ መካኒካል አየር ማናፈሻና ማቀዝቀዣ ዲዛይን አግባብነት ባለውና በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ መሠረት መሰራት ይኖርበታል። እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑንና በስታንዳርዱ መሠረት መስራቱን ማረጋገጥ አለበት።

4.8.9.6 ማንኛውም ሕንፃ በዲዛይኑና ግንባታ ሂደቱ የእሳት አደጋን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ሲሆን፤ በዲዛይን ወቅት የእሳት አደጋ ማምለጫ እና የሕንፃው መዋቅራዊ አካላት እሳትን መቋቋም ስለመቻላቸው በተሻሻለው የህንፃ ስታንዳርድ መሠረት መሰራት ይኖርበታል። እንዲሁም ዲዛይን አጽዳቂውም የቀረበው ዲዛይን የተሟላ መሆኑንና በስታንዳርዱ መሠረት መስራቱን ማረጋገጥ አለበት።

3. በመመሪያው አንቀፅ 6 ስር የሚገኘው ንዑስ አንቀፅ 6.2.1 ድንጋጌ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 6.2.1 ተተክቷል።

6.2.1 ከሪልስቴት ውጪ ላሉ በምድብ "ሀ" ህንጻ ስር ለሚካተቱ የሕንፃ የዲዛይኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ 5 የሥራ ቀናት ያልበለጠ ይሆናል፡፡

4. የመመሪያው አንቀፅ 7 ንኡስ አንቀፅ 7.4 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ ዓንቀፅ 7.4 ተሻሽሎ ተተክቷል፦

7.4 ደረጃ በደረጃ ወይም በየምዕራፉ ለመገንባት የቀረበ ዲዛይን ወይም ፕላን በተመለከተ፦

7.4.1 የመጀመሪያው የግንባታ ደረጃ ህንፃው ከሚያርፍበት ከተማ ወይም አከባቢ መሪ ኘላን ዝቅተኛ መስፈርትና የሕንፃ ከፍታ ደረጃ ሳያንስ የግንባታ ፈቃድ ሊሰጥ ወይም ሊፀድቅ ይችላል፡፡

7.4.2 ለክትትልና ለመጠቀሚያ ምስክር ወረቀት አሠጣጥ ያመች ዘንድ በግንባታ ፈቃድ ሰነድ ላይ ደረጃ በደረጃ ለመገንባት የታቀደው በግልፅ ተለይቶ በሚፈቀደው ዲዛይን ወይም ፕላን ላይ መመልከት ይኖርበታል፡፡

7.4.3 የዚህ መመሪያ ዓንቀፅ 7.4.1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በከተማው ወይም የአከባቢው መሪ ፕላን ዝቅተኛ መስፈርትና የህንፃ ከፍታ ለማይገደዱ አገልግሎቶች የሚውሉ ህንፃዎች ላይ የብሎኮችን መጠን ወይም ብዛት ደረጃ በደረጃ በመወሰን ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7.4.4 ደረጃ በደረጃ የግንባታ ፈቃድ ወስዶ የመጀመሪያውን ምዕራፍ አጠናቆ የመጠቀሚያ ፈቃድ ወስዶ አገልግሎት ላይ የዋለን ሕንፃ ቀጣይ ምዕራፍ ለመጀመር ካስፈለገ በቀሪው የህንፃው አካል ላይ ግንባታ እየተከናወነ ቀድሞ የተጠናቀቀው የህንፃው ክፍል አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑን እና በአካባቢው እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሰዎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ የማይችል መሆኑን በማረጋገጥ የቀጣይ ግንባታ ፈቃድ መሰጠት አለበት፡፡ ስለሆነም በግንባታ ወቅት በአካባቢው የሚንቀሳቀስ ሰው ከአደጋ ለመከላከል ገንቢው ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰዱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በግንባታ ሂደቱ ለሚደርስ አደጋ አሰሪው፣ ገንቢውና አማካሪው የጋራ ወይም የተናጠል ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡

7.4.5 አሰሪው የቀጣይ ምዕራፍ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ለክትትልና መጠቀሚያ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እንዲያመች ለሕንፃ ሹሙ በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፡፡

5. የመመሪያው አንቀፅ 8 ንኡስ ዓንቀፅ 8.1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 8.1 ተሻሽሎ ተተክቷል፦

8.1 ከህንፃ አዋጁ፣ ከደንቡ፣ ከዚህ መመሪያ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርዶች ጋር የማይጣጣም የግንባታ ዲዛይን በህንፃ ሹሙ ውድቅ ይደረጋል፡፡

6. በመመሪያው ዓንቀፅ 10 ስር ከንዑስ አንቀፅ 10.7.3 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ 10.7.4 ተጨምሯል፦



የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር * የረጋርድና ማዘዣ አገልግሎት *

አይሻ መሐመድ ሙሳ (ኢ/ር)
ሚኒስትር

10.7.4 አሰሪው ከተፈቀደለት ዲዛይን ወጪ እየሰራ ቢገኝ፤ የሕንፃ ግንባታ ፈቃዱ ይታገዳል፡፡

7. በመመሪያው አንቀፅ 11 ንዑስ ዓንቀፅ 1 ስር ከ 11.1.8.4 ቀጥሎ ሶስት አዳዲስ ንዑሳን አንቀፆች 11.1.8.5፣ 11.1.8.6 እና 11.1.8.7 ተጨምረው እንደሚከተለው ተካተዋል፦

11.1.8.5 ወሰንተኛው በግንባታው ወሰን ያለው መብቱ መከበሩንና በግንባታ ወቅት የሚወሰዱትን ጥንቃቄዎች አሠሪው እንደሚወስድ ግዴታ መግባቱን አረጋግጦ የወሰን ላይ ግንባታ ስምምነት የመፈረም ኃላፊነት አለበት፡፡ ቅፁን ለመሙላት ፈቃደኛ በማይሆን ወሰንተኛ ህንፃ ሹሙ ወይም ለዚህ ስራ የተሰየመው አካል ቅፁን የማስሞላት ሃላፊነት ያለበት ሲሆን ወሰንተኛው ፈቃደኛ ባይሆን ያልፈረመበትን ተጨባጭ ምክንያት በጽሑፍ ለሕንፃ ሹሙ በ3 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ያቀርባል፡፡ የህንጻ ሹሙ የቀረበውን ቅሬታ በመመርመር እንዲሁም ወሰንተኛው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ባያቀርብ እንኳን ግንባታው መብቱን የማይነካ መሆኑን በማረጋገጥ ያለወሰንተኛ ስምምነት የወሰን ላይ ግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

11.1.8.6 በግንባታው ወሰን ላይ የተሰጠው መረጃ ወይም ግንባታ ፈቃድ ትክክለኛ አይደለም በማለት ወሰንተኛው ፈቃዱን ለሰጠው አካል ቅሬታውን ካቀረበ፤ የህንፃ ሹሙ ወይም ለዚህ ስራ የተሰየመ የመንግስት አካል የቀረበውን ቅሬታ አግባብነት ካላቸው መረጃዎች ጋር በማገናዘብ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

11.1.8.7 በሚገነባው ህንፃ ያለው አዋሳኝ የታወቀ ባለይዞታ የሌለው ወይም የመንግስት ክፍት ቦታ ከሆነ፤ ህንፃ ሹሙ ወይም በአከባቢው አስተዳደር የተሰየመው አካል በዚህ መመሪያ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት የአዋሳኝ ስምምነትን በተመለከተ የተደነገጉ ድንጋጌዎች መከበራቸውን በማረጋገጥ የግንባታ ፈቃድ መስጠት አለበት፡፡

8. የመመሪያው አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 11.1.10.4 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 11.1.10.4 የተተካ ሲሆን፤ ከዚሁ ድንጋጌ ቀጥሎ የሚከተሉት ሁለት አዳዲስ ንዑስን አንቀፆች 11.1.10.5 እና 11.1.10.6 ተጨምረው ተካተዋል፦

11.1.10.4 የወሰን ላይ ግንባታ ጉዳት እንዳያደርስ መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ ጥንቃቄዎች መወሰድ አለባቸው፡፡ በማንኛውም የወሰን ላይ ግንባታ ሂደት ለሚፈጠር ችግር አሠሪው ሙሉ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ እንዲሁም መወሰድ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎች ተወስደው ያልታሰበ ችግር ቢፈጠር አሠሪው አስፈላጊው የእርምት እርምጃ መውሰድ አለበት፤



የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
ሚኒስትር

11.1.10.5 አሰሪው በተፈቀደው የወሰን ላይ ግንባታ ዲዛይን መሠረት ግንባታው ስለመከናወኑ ኃላፊነት አለበት፤

11.1.10.6 በወሰን ላይ ግንባታ የመሠረት ቁፋሮ ሲከናወን በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ ES 3965 Occupational Health and Safety ክፍል 6 መሠረት መከናወን አለበት::

9. በመመሪያው አንቀፅ 11 ከንዑስ ዓንቀፅ 11.3.6 ቀጥሎ የሚከተሉት አምስት አዳዲስ ንዑስ አንቀፆች 11.3.7፣11.3.8፣11.3.9፣11.3.10 እና 11.3.11 ተጨምረው ተካተዋል፡-

11.3.7 የግንባታ ማፍረስ ሥራ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ "ES 3965 Occupational Health and Safety" ክፍል 8 መሠረት መከናወን አለበት::

11.3.8 በህንፃ ‹‹ምድብ "ለ" እና "ሐ"›› ስር የሚካተቱ ህንፃዎች የማፍረስ ስራ በሚመለከተው አካል ተመዝግቦ የማፍረስ ፈቃድ (Demolition work Premit) በተሰጠውና የታደሰ ፈቃድ ባለው አካል መከናወን አለበት።

11.3.9 ተገቢነት ያላቸውን አባሪ ሰነዶች አሟልቶ ግንባታን ለማፍረስ የሚቀርብ ጥያቄ በ3 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ሊሰጠው ይገባል።

11.3.10 የማፍረስ ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ አልሚው ፈቃዱን ለሰጠው አካል ሪፖርት በማድረግ በተሰጠው ፈቃድ ልክ ማከናወኑን እንዲረጋገጥ ማስቻል አለበት።

11.3.11 የተሰጠው ፈቃድ አንድን ግንባታ ሙሉ በሙሉ ለማፍረስ ከሆነ የሚፈርሰው ህንፃ ሰነድ ግልባጭ በከተማው ወይም በአከባቢው ቋሚ ንብረት ለሚመዘግበው ወይም የመሬት ይዞታን ለሚያስተዳድረው የመንግስት አካል ይሰጣል።

10. የመመሪያው አንቀፅ 17 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 17 ተሻሽሎ ተተክቷል፡-

17. ስለ ተቆጣጣሪዎችና የግንባታ ክትትል

17.1 ስለ ተቆጣጣሪዎች

17.1.1 ማንኛውም ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ የያዘ የህንፃ ሹም ወይም በአከባቢው አስተዳደር የተሰየመ አካል የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ወይም ግንባታ በሚከናወንበት በማንኛውም ጊዜ እንዲሁም የምሽት ግንባታ ካለ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ በግንባታው ቅጥር ግቢ ተገኝቶ የቁጥጥር ሥራ ማከናወን ይችላል።ያከናወነውን የቁጥጥር ተግባር የሰጠውን ትዕዛዝ የግንባታ መከታተያ ቅጽ 13 በመሙላት ለሕንጻ ሹሙ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል።

17.1.2 በማንኛውም ወቅት ወደ የትኛውም ይዞታ ለክትትልና ቁጥጥር ተግባር የሚንቀሳቀስ የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በዕለቱ ወደ ግንባታ ቦታ መግባት ያስፈለገበትን ምክንያት እና በግንባታው ቦታ ተገኝቶ ያከናወነውን የቁጥጥር ሥራ ዝርዝር፣ የተገኘውን ውጤትና የሰጠውን ለተቆጣጣሪዎች በተለየ እና

በግንባታ ቦታ በሚቀመጥ የቁጥጥር መዝገብ ላይ ሞልቶ በማስፈረምና በመፈረም ቅጂውን ለግንባታው ባለቤት ወይንም በግንባታው ቦታ ለሚገኝ ተጠሪ መስጠት አለበት፣ የቁጥጥር መዝገብ ተከታታይ ዋና እና ቀሪ የገጽ ቁጥር፣ የትእዛዝ መስጫ ቦታ፣ የስኬች መስሪያ ቦታ፣ ለተቆጣጣሪ ለሥራ ተቋራጭ እና ለአማካሪ የፊርማ ቦታ የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

17.1.3 የሕንጻ ተቆጣጣሪው የሕንፃ አዋጁን፣ የሕንጻ ደንቡን፣ ይህን መመሪያ፣ ህንፃ ስታንዳርዶች እና ተጓዳኝ ሕጎችንና ውሎችን በመተላለፍ የሚካሄድ ግንባታ እንዲቆም ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ የማስቆሚያ ትዕዛዝ የሚሰጠው በአንቀጽ 17.2 ላይ በተመለከተው መሠረት እና የግንባታ ማስቆሚያ ቅጽ 015 በመሙላት ይሆናል፡፡

17.1.4 ያለምንም የፅሑፍ ማስታወሻ የሚደረግ የግንባታ ቦታ ጉብኝትም ሆነ የሚሰጥ የቃል ትዕዛዝ ህጋዊነት አይኖረውም፡፡

17.1.5 የህንፃ ሹሙ ወይም የሚወክለው አካል ከግንባታው ባለቤት የግንባታውን ክትትልና ቁጥጥር ሥራ አስመልክቶ ለሚቀርብለት ማስታወቂያ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ በግንባታ ክትትል ውሳኔ መግለጫ ቅጽ 016 በመሙላት መልስ መስጠት ይኖርበታል፡፡

17.2 ግንባታ ክትትል

17.2.1 "ለክትትል" ተብሎ የተሰጠው የግንባታ ፈቃድ ሰነድ ግንባታው በሚካሄድበት ቦታ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ በግልጽ ቦታ ላይ መቀመጥ አለበት፡፡

17.2.2 ማንኛውም የግንባታ ፈቃድ የያዘ ገንቢ ግንባታ ከመጀመሩ ከ 3 የስራ ቀናት በፊት ግንባታ ፈቃዱን ለሰጠው መስሪያ ቤት የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ክፍል ግንባታ ሊጀምር መሆኑን በማሳወቅ የክትትል የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የግንባታ ማስጀመሪያ ማረጋገጫ መውሰድ አለበት፡፡

17.2.3 እንደ ሥራው ዓይነት እና የአሠራር ዘዴ በሕንፃ ሹሙ የሚጠየቁ ተጨማሪ እርከኖች ክትትል መደረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ መደበኛ ክትትል የሚደረግባቸው የግንባታ ደረጃዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፡-

ሀ) ግንባታ ለመጀመር ማንኛውም የቅየሳ ስራ ተጠናቆ ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊት፤

ለ) የመሠረት ቁፋሮ ከተጠናቀቀና የመሠረት ብረቶችና ፎርምወርክ በቦታቸው ከተቀመጡ በኋላ፤

ሐ) የምድር ወለል ብረቶች፣ የፍሳሽ ማስወገጃና የሀርድ ኮር ሙሌት ከተከናወነ በኋላ፤

መ) የወለል ቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረቶች እና ፎርምወርክ ስራ ከተከናወነ በኋላ፤

ሠ) የየፎቁ ወለል ብረቶች፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ ኤሌክትሪካል መስመር ዝርጋታና የፎርምወርክ ስራ እንዲሁም የቋሚ ተሸካሚ አካላት ብረቶችና ፎርምወርክ ስራ ከተከናወነ በኂላ፤

ረ) የውሃ አቅርቦት፣ የሳኒታሪ፣ የኤሌክትሪክ እና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ገጠማ ተጠናቆ ፍተሻ በሚደረግበት ጊዜ፣

ሰ) የጣሪያ ስላብ(ሶሌታ) ማጠናቀቂያ ወይም የጣሪያ ሽፋን ስራ ከመከናወኑ በፊት፤

17.2.4 መደበኛ ክትትል በሚደረግባቸው የግንባታ ደረጃዎች ገንቢው ለሚመለከተው የክትትል ክፍል ሳያሳውቅና ስራን ለመቀጠል ፈቃድ ሳያገኝ ግንባታውን ማከናወን የለበትም፤

17.2.5 በማንኛውም ግንባታ ላይ የሚቀርብ የግንባታ ጥሬ እቃዎችና የሚመረቱ የግንባታ ቁሶች የግንባታ ጥራትና ደረጃ መስፈርት ያሟሉ መሆን አለባቸው፤

17.2.6 በየእርከኑ ለሚከናወኑ የኮንክሪት ስራዎች የኮንክሪት ናሙና መወሰድ አለበት፣የተወሰዱት የኮንክሪት ናሙናዎች ቀነ ገደባቸውን ጠብቆ ፈቃድ ባለው ላብራቶሪ በማስመርመር ውጤቱን ለተቆጣጣሪው አካል ማሳወቅ አለበት፤

17.2.7 የግንባታ መስፋፋትንና የህንጻ ከፍታን የማያካትት የዲዛይን ለውጥ ማስታወቂያ የደረሰው የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ክፍል በሰነዱ ላይ የተመለከተው ለውጥ የማይፈቀድ ወይም በቅድሚያ የግንባታ ፈቃድ እንዲወጣ የሚጠይቅ ከሆነ ማስታወቂያው በደረሰው በ 3 ቀን ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን ለግንባታው ባለቤት ወይም ለአማካሪው ወይም ለተቋራጩ ያሳውቃል፤

17.2.8 በግንባታ ወቅት ጤናንና ደህንነትን ለማረጋገጥ በግንባታው ሂደት ላይ የሚሳተፉት በሙሉ ተሻሽሎ ስራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ የሥራ ላይ የጤናና ደህንነት ሰነድ መሠረት ስራቸውን ማከናወን ይኖርባቸዋል።

17.2.9 የፕሮጀክቱ ሥራ ተቋራጭ በግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሠራተኞች ጤናና ደህንነት ለማስጠበቅ ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት እንደስራው ዓይነት መውሰድ የሚገባቸው ጥንቃቄ ተገቢው ግንዛቤ ማስጨበጥ አለበት።

17.2.10 የፕሮጀክቱ ሥራተቋራጭ በግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሠራተኞች ጤናና ደህንነት ለማስጠበቅ አስፈላጊ አልባሳት ማሟላት አለበት'አማካሪውም ይህ መሟላቱን መከታተል ይኖርበታል'እንዲሁም የሕንጻ ሹሙም ተወካይ ሁሉም አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ማረጋገጥ አለበት'ያልተሟላ ከሆነ ተገቢውን ማስተካከያ እንዲደረግ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ይገባዋል።



የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

11.በመመሪያው አንቀፅ 19 ከንዑስ ዓንቀፅ 19.4 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀፅ 19.5 ተጨምሮ እንደሚከተለው ተካቷል፡-

19.5 የህንፃ ሹም ደህንነቱ አስጊ አለመሆኑን ለተረጋገጠ እና በከፊል ለተጠናቀቀ ሕንፃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል። በከፊል ለተጠናቀቀ ሕንፃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሲሰጥ የሚከተሉትን መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

19.5.1 ጥቅም ላይ ከሚውሉት የህንፃው ክፍሎች ውጪ ያለው የህንፃው ቀሪ አካል ግንባታ ስራ መቆሙን፤

19.5.2 ሕንፃው መዋቅራዊ አካል እና ግድግዳዎች መጠናቀቃቸውን፤

19.5.3 ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡት የሕንፃው ፎቆች ደረጃቸው የድጋፍ መያዣ ሙሉ በሙሉ መገጠማቸው እና ያልተጠናቀቁ የሕንፃው ፎቆች ጥቅም ላይ ለማዋል ከታሰቡት ለመለየት ጊዜያዊ ከለላ የተደረገላቸው ስለመሆኑ፤

19.5.4 የሕንፃው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ከፍሳሽ ማስወገጃ ጋር መገናኘቱን እና ጥቅም ላይ ለማዋል የታሰቡት መፀዳጃ ቤቶች ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቃቸውን፤

19.5.5 የሕንፃው የውሃ መስመር ጥቅም ላይ ለማዋል ለታሰበው ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁንና ውሃ መዳረሱን ፤

19.5.6 የሕንፃው የኢሌክትሪክ መስመር ጥቅም ላይ ለማዋል በታሰቡት ክፍሎች ላይ ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁንና መዳረሱን እንዲሁም ጥቅም ላይ የማይውለው የሕንፃው ክፍል የኤሌትሪክ ኃይል አደጋ እንዳያደርስ አስፈላጊው ጥንቃቄ መደረጉን፤

19.5.7 የሕንፃው ያልተጠናቀቀው ክፍል ለማጠናቀቅ በሚደረገው ሂደት ሕንፃውን በሚጠቀሙ እና በሕንፃው በኩል በሚያልፉ መንገደኞች ላይ አደጋ እንዳይደርስ ተሻሽሎ ስራ ላይ በዋለው የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ የሥራ ላይ የጤናና ደህንነት ሰነድ መሠረት መወሰድ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች መወሰዳቸውን፤

19.5.8 ሕንፃው በዲዛይኑና ተሻሽለው ስራ ላይ በዋሉት የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርዶች መሠረት የእሳት አደጋ ጊዜ ማምለጫዎች መጠናቀቃቸውንና ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን ፈትሾ በማረጋገጥ፤

19.5.9 ህንፃው ለአካል ጉዳተኞች ከእንቅፋት የፀዳ መዳረሻ መንገድ ገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት ያደረገ መሆኑን፤

19.5.10 የሕንፃው አመላካች የሆኑ ምልክቶች አገልግሎት ሲሰጡ በታቀዱት ሁሉ መቀመጣቸውና አገልግሎት ላይ መዋላቸው በማረጋገጥ፤

19.5.11 የእሳት አደጋ መከላከያ ስፕሪክለር ካለው በአግባቡ መገጠሙንና መስራቱን በማረጋገጥ፤

19.5.12 የሕንፃው የውሃ አቅርቦትና ለእሳት አደጋ መከላከያ የሚሆን ውሃ አቅርቦት የሚሆን ውሃ ፓምፕ መገጠሙንና መስራቱን ማረጋገጥ ይሆናል።

12.የመመሪያው አንቀፅ 27 ንዑስ ዓንቀፅ 27.7 ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ 27.7 ተሻሽሎ እንደሚከተለው ተተክቷል፦

27.7 የህንጻ ግንባታዎች ከፍታ እንዲሁም ከመንገድ ዳር ሊኖራቸው የሚገባ ርቀት በተመለከተ የከተማው ፕላን እና አግባብነት ያላቸውን ማስፈፀሚያ የሕግ ማዕቀፎቹ በሚያስቀምጡት መስፈርት መሰረት የሚፈፀም ይሆናል።

13.የመመሪያው አንቀፅ 28 ንዑስ ዓንቀፅ 28.2.1(መ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 28.2.1 (መ) ተሻሽሎ ተተክቷል፦

28.2.1 (መ) የውጭ ገፅታ ኘላን (Elevation)

በዲዛይኑ የውጭ ገፅታ ኘላን የሁሉንም የህንፃ ገፅታዎች የሚያሳይ መሆን አለበት። ሙሉ በሙሉ የማይታይና በሌላ ሕንፃ የተሸፈነ የውጭ ገፅታ በተቀረጠ የቁም ገጽታ ኘላን (Section plan) መታየት አለበት።

በውጪ ገፅታ በኩል የሚቀመጡ መስታወቶች ወይም ከመስታዎት የተሰሩ የውጪ ግድግዳዎች አንፀባራቂ አለመሆናቸው በዲዛይኑ መገለፅ ያለበት ሲሆን፤ የመስታዎት ግድግዳዎቹ ለአካባቢ ደህንነትና ጤንነት ተፅዕኖ የማይፈጥሩ እንዲሁም ለነዚህ ግብዓቶች በሚመለከተው አካል የፀደቀ የአገሪቷ ስታንዳርድ መስፈርት የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

14. የመመሪያው አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀፅ 28.3.11 ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ 28.3.11 እንደሚከተለው ተሻሽሎ ተተክቷል፦

28.3.11 የመሠረት አፈር ምርመራ

ሀ) የመሠረት አፈር ምርመራ መከናወን ያለበት ሥልጣን ባለው የመንግስት አካል ተመዝግቦ ፈቃድ በተሰጠው ኩባንያ ወይም ድርጅት መሆን አለበት፤

ለ) የአንድ ኘሮጀክት የግንባታ ቦታ የአፈር ጥናት ተካሂዶ የሚቀርብ የላቦራቶሪ ውጤት ለምርመራ የሚጠቀምባቸውን ስታንዳርዶች አግባብነት ያላቸውና ተሻሽለው ስራ ላይ የዋሉት የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርዶች ማጣቀሻ፣ የአፈር ምርመራና የመሸከም ውጤት መግለጫ፣ የመሠረት ዲዛይን ዓይነት አማራጭ ጥቆማ፣ ሌሎች የተለዩ ከምድር በታች ያለ የህንፃ አካላት ዲዛይን አሠራር ጥቆማ የያዘ መሆን ያለበት

ሲሆን፤ ከሪፖርት ጋር የብቃት ማረጋገጫ እና የታደሰ የንግድ ፈቃድ ቅጂ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

15. የመመሪያው አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ 33.3.1 ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ 33.3.1 እንደሚከተለው ተሻሽሎ ተተክቷል፡-

33.3.1 ማንኛውም ተዳፋት ወይም ራምፕ ተዳፋቱ ከ 4.5% ያልበለጠ ሆኖ ከዋናው ወለል ማከፋፈያ መተላለፊያ (lobby) ወይም የወለል መዳረሻ ጋር መገናኘት ይኖርበታል፤

16. የመመሪያው አንቀፅ 35 ንዑስ አንቀፅ 35.1.1 ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ 35.1.1 እንደሚከተለው ተሻሽሎ ተተክቷል፡-

35.1.1 ማንኛውም መወጣጫ (Scaffolding) መሸከም በሚገባው ክብደት መጠን መሠረት ዲዛይን ተደርጎ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን፤ ለማንኛውም ከምድር በላይ 6 ፎቅ እና በላይ ለሆነ ህንጻ ግንባታ የሚውሉ መወጣጫ (Scaffolding) በተለምዶ ጥቅም ላይ ከሚውሉት አጠና እና ጣውላ ቁስ ውጪ በተገጣጣሚና ተነቃቃይ ብረት ቁስ የተሰሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

17. የመመሪያው አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀፅ 41.2.2 ተሰርዞ በአዲስ ንኡስ አንቀፅ 41.2.2 እንደሚከተለው ተሻሽሎ ተተክቷል፡-

41.2.2 ማንኛውም ሕንፃ በእሳት አደጋ ጊዜ ከአደጋ ነፃ ወደ ሆነው ቦታ ለመውጣትና ለማምለጥ የሚያስችሉ በእያንዳንዱ ፎቅ ላይ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ህንፃ ስታንዳርድ "ES 3964 Fire Precautions During Building Construction Design, Works and use" ክፍል 3 መሠረት የእሳት አደጋ ማምለጫ መንገዶች ሊኖሩት ይገባል፤

3. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማሻሻያ መመሪያ ከ ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ግንቦት 2010 ዓ.ም

አይሻ መሐመድ (ኢንጂነር)
የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚንስትር